# የኢፌዲሪ ፍትህ ሚኒስቴር የዓቃቤ ሕግ ፈተና

## Part I: Choice (1% Each)

**1. ዐቃቤ ህግ በህግ መሰረት የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር ሲያከናውን ለሚደርስ ጉዳት የህግ ተጠያቂነት የለበትም፡፡**

ሀ. እውነት

ለ. ሐሰት

**2. በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ መሰረት በግልግል ዳኝነት በተወሰነ ጉዳይ ላይ ይግባኝ ማቅረብ አይቻልም።**

ሀ. እውነት

ለ. ሐሰት

**3. የኢትዮጵያ የባህር ህግ ኢትዮጵያ የባህር ወደብ የሌላት ሀገር ከሆነችበት ጊዜ አንስቶ ተፈጻሚነቱን አጥቷል፡፡**

ሀ. እውነት

ለ. ሐሰት

**4. በአስር ዓመታት ውስጥ የሞት ፍርድ ቅጣት በኢትዮጵያ አለመፈጸሙ በኢትዮጵያ የሞት ፍርድ ቀሪ መደረጉን ያሳያል፡፡**

ሀ. እውነት

ለ. ሐሰት

**5. ፍትህ ሚኒስቴር በሀገሪቱ በሚገኙ ፍርድ ቤቶች የፍትሐ ብሔር ክርክር ለማድረግ የገንዘብ አቅም የሌላቸው ዜጎች የህግ ድጋፍ እንዲደረግላቸው ጥያቄ ሲያቀርቡ ወክሎ ክርክር የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡**

ሀ. እውነት

ለ. ሐሰት

**6. በፌዴራል ህገ መንግስት መሰረት ክልሎች ህግ ሊያወጡ የሚችሉበት ጉዳይ የትኛው ነው?**

ሀ. የኢምግሬሽን ጉዳይ

ለ. የጦር መሳሪያ ቁጥጥርና አስተዳደር

ሐ. የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም

መ. የወንጀል ጉዳይ

ሠ. ሀ እና ለ

ረ. መልስ አልተሰጠም

**7. ከሚከተሉት ውስጥ ስህተት የሆነውን ምረጡ?**

ሀ. የፌዴራል መንግስት ሰራተኞች ህግ

ለ. የፌዴራል የአሰሪና ሰራተኛ ህግ

ሐ. የክልል መንግስት ሰራተኞች ህግ

መ. የክልል የአሰሪና ሰራተኛ ህግ

ሠ. ሀ እና ሐ

ረ. ለ እና መ

ሰ. መልስ አልተሰጠም

**8. ከሚከተሉት የመንግስት ተቋማት ውስጥ የህግ አስፈጻሚው አካል የሆነው የቱ ነው?**

ሀ. የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን

ለ. ምርጫ ቦርድ

ሐ. ዋና ኦዲተር

መ. የህዝብ ቆጠራ ኮሚሽን

ሠ. ሐ እና መ

**9. በኢትዮጵያ የህጎች ተዋረድ (hierarchy of laws) ከታች ወደ ላይ ትክክለኛው ቅደም ተከተል የቱ ነው?**

ሀ. ደንብ (Regulation)፣ መመሪያ (Directive)፣ አዋጅ (Proclamation)፣ ህገ መንግስት

ለ. ደንብ፣ አዋጅ፣ መመሪያ፣ ህገ መንግስት

ሐ. መመሪያ፣ አዋጅ፣ ደንብ፣ ህገ መንግስት

መ. መመሪያ፣ ደንብ፣ አዋጅ፣ ህገ መንግስት

ሠ. ህገ መንግስት፣ አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ

**10. ከሚከተሉት ውስጥ በ2013 ዓ.ም በወጣው የንግድ ህግ ውስጥ ያልተካተተው የቱ ነው?**

ሀ. የሽርክና ማህበር (Joint Venture)

ለ. የህብረት ሽርክና ማህበር (General Partnership)

ሐ. ተራ የሽርክና ማህበር (Ordinary Partnership)

መ/ ሁለት አይነት ኃላፊነት ያለበት የሽርክና ማህበር (Limited Partnership)

**11. ከሚከተሉት ውስጥ ሁሌም ድንበር ተሻጋሪ (Transnational) የሆነው የቱ ነው?**

ሀ. የሽብር ወንጀል (Terrorism)

ለ. በሰው የመነገድ ወንጀል (Human Trafficking)

ሐ. ሰውን በህገ ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር (Smuggling of Persons)

መ. በወንጀል የተገኘን ሀብት/ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ (Money Laundering)

ሠ. መልስ አልተሰጠውም

**12. በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ መሰረት በቸልተኝነት ሲፈፀም የማያስቀጣው የቱ ነው?**

ሀ. ማነሳሳት (Incitement)

ለ. አባሪነት (Accomplice)

ሐ. ሙከራ (Attempt)

መ. ሁሉም መልስ ናቸው

**13. ከዚህ በታች ከተመለከቱት መካከል የወንጀል ክስ ለማቅረብ ስልጣን ያለው ተቋም የትኛው ነው?**

ሀ. የፌዴራል ስነ ምግባር እና ፀረ ሙስና ኮሚሽን

ለ. የገቢዎች ሚኒስቴር

ሐ. የፍትህ ሚኒስቴር

መ. የንግድ አሰራር እና ሸማቾች ሙብት ጥበቃ ባለስልጣን

ሠ. ሀ እና ሐ

ረ. ሁሉም መልስ ነው

**14. በወንጀል የማያስቀጡ እና ይቅርታ የሚያሰጡ ሁኔታዎች ውስጥ ያልሆነው የትኛው ነው?**

ሀ. የግል ተበዳይ ባለሙብት በማንኛውም ወንጀል በተበዳይ ፈቃድ የተፈጸመ የወንጀል ድርጊት ሲሆን

ለ. አንድ ወታደር በበላይ አማካኝነት በተሰጠ ግልጽ ትዕዛዝ የተፈጸመ ማንኛውም የወንጀል ድርጊት ሲሆን

ሐ. በማንኛውም ሁኔታ በቴክኒካዊ ፍሬ ነገር ሁኔታ የተሳሳተ ግንዛቤ ተይዞ የተፈጸመ የወንጀል ድርጊት ሲሆን

መ. ሁሉም መልስ ነው

ሠ. መልስ የለም

**15. የሞት ቅጣትን በተመለከተ በወንጀል ህጉ ያልተመለከተው የትኛው ነው?**

ሀ. የሞት ቅጣት የሚወሰነው እድሜው 18 አመት በሞላው ወንጀለኛ ላይ ብቻ ነው

ለ. የሞት ቅጣት በስቅላት ሊፈጸም ይችላል

ሐ. የሞት ቅጣት በማረሚያ ቤት ግቢ ውስጥ ሊፈጸም ይችላል

መ. መልስ የለም

**16. ከሚከተሉት ውስጥ የፍትህ ሚኒስቴር አላማ ያልሆነው የትኛው ነው?**

ሀ. የፌዴራል እና የክልል መንግስታትን እንዲሁም የህዝብን የፍትሐብሄር ጥቅም ማስከበር

ለ. ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን ማክበርና ማስከበር

ሐ. የወንጀል ህግን ማስከበር

መ. የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ

ሠ. መልስ የለም

**17. ከሚከተሉት ውስጥ በኢትዮጵያ የህግ ማዕቀፍ ውስጥ ወንጀል ሆኖ ያልተደነገገው የቱ ነው?**

ሀ. ወረራ (Aggression)

ለ. ኢ-ሰብአዊ አያያዝ (Torture)

ሐ. ዘር ማጥፋት (Genocide)

መ. በሰብአዊነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች

ሠ. ሀ እና መ

ረ/ ከ"ሐ" በስተቀር ሁሉም መልስ ናቸው

**18. የወንጀል ጉዳይን በመከላከል ረገድ (Defense in Criminal Law) የማያስቀጡ ሁኔታዎች ከተባሉት መካከል፡**

ሀ. ሕፃንነት

ለ. ስካር

ሐ. አስገዳጅ ሁኔታ

መ. የበላይ ትዕዛዝ

ሠ. ሁሉም መልስ ናቸው

**19. ከሚከተሉት አለም አቀፍ ስምምነቶች አንዱ ልዩ ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው የተወሰኑ የህብረተሰብ ክፍላትን የሚመለከት አይደለም፡**

ሀ. የሕፃናት መብት ኮንቬንሽን

ለ. በሴቶች ላይ የሚፈጸም ማንኛውም ዓይነት መድልዎ ለማስወገድ የተፈረመው ኮንቬንሽን

ሐ. የአካል ጉዳተኞች መብት ኮንቬንሽን

መ. ሰዎችን ተገዶ ከመሰወር ለመከላከል የተፈረመው ኮንቬንሽን

ሠ. መልስ አልተሰጠም

**20. በተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን የተቀበለውና በአንድ ሀገር ውስጥ ያሉ ልዩ ሁኔታዎችን ወይም በሁሉም የዓለም ክፍሎች ያሉ ጭብጥ ጉዳዮችን (thematic issues) ለመከታተል በኮሚሽኑ የሰብዓዊ መብት ጉባኤ (Human Rights Council) የሚተገበረው ዘዴ፡**

ሀ. የግል አቤቱታ (Individual Complaint)

ለ. ልዩ ሥነ-ስርዓት (Special Procedure)

ሐ. ሀገራዊ ሪፖርት (State Report)

መ. የጎንዮሽ ሪፖርት (Shadow Report)

**21. ከሚከተሉት መካከል በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት ፍጹም የሆነ መብት ተደርጎ የሚወሰደው የትኛው ነው?**

ሀ. የአካል ደህንነት መብት

ለ. ኢሰብአዊ አያያዝ የመጠበቅ መብት

ሐ. በባርነት ያለመያዝ መብት

መ. ሁሉም መልስ ናቸው

**22. ከሚከተሉት ውስጥ ተጠርጣሪ ተላልፎ እንዲሰጥ የሚጠይቅ ሀገር ሊያሟላ የሚገባው የትኛውን ነው?**

ሀ. ተጠርጣሪው የተጠረጠረበት የወንጀል ጉዳይ በበቂ ሁኔታ ክብደት ያለው መሆኑ

ለ. በተጠርጣሪው ላይ ክስ ለመመስረት የሚያስችል ቅድመ ሁኔታዎች መሆናቸውን (existence of prima facie case)

ሐ. ተጠርጣሪው በጠየቀው ሀገር የፍትህ ሥርዓት ሂደት በፍትሃዊነት ሊዳኝ የሚችል ስለመሆኑ ዋስትና

መ. ተጠርጣሪው ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ የሚጣልበት ቅጣት ከወንጀሉ ጋር ተመጣጣኝ እንደሚሆን ማረጋገጥ

ሠ. ሁሉም መልስ ናቸው።

**23. ለዓለም አቀፍ የህግ /የፍትህ/ ትብብር በተለይም ለአሳልፎ መስጠት መሰረቶች**

ሀ. ዓለም አቀፍ ስምምነቶች

ለ. ዓለም አቀፍ የልማድ ህግ

ሐ. የጋራ በጋራ (reciprocity) መርህ

መ. የውስጥ (ብሔራዊ) ህጎች

ሠ. ሀ እና ለ

ረ. ሁሉም መልስ ናቸው፡፡

ሰ. መልስ አልተሰጠም

**24. አሳልፎ መስጠት የሚመሳሰለው ከየትኛው ጋር ነው**

ሀ. አንድን የሌላ ሀገር ዜጋ ከሀገር ማስወጣት (deportation or expulsion)

ለ. ፍርደኛን ማስተላለፍ (transfer of sentenced persons)

ሐ. ሀ እና ለ

መ. መልስ አልተሰጠም

**25. ከሚከተሉት ትክክል ያልሆነው የትኛው ነው?**

ሀ. በብሔራዊ ባንክ የምንዛሪ ተመን ያልወጣላቸው የውጭ ሀገር ገንዘቦችን ይዞ መገኘት የወንጀል ተጠያቂነትን ያስከትላል

ለ. ከፍቃድ ውጭ ማንኛውም የውጭ ምንዛሪ ይዞ መገኘት የወንጀል ተጠያቂነት ያስከትላል

ሐ. በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ መገበያያ ሆኖ የማያገለግል የውጭ ገንዘብ ያለ ፈቃድ መያዝ የወንጀል ተጠያቂነትን ያስከትላል

መ. መልስ አልተሰጠም

**26. የአስገድዶ መድፈር የወንጀል ድርጊት የተፈጸመባት የወንጀል ተጎጂ በዚሁ ጥቃት ምክንያት ወዲያውኑ ህይወቷ ቢያልፍ አጥፊው:**

ሀ. በአስገድዶ መድፈር እና በሰው መግደል ወንጀል ተደራራቢ ሁለት ክስ ይቀርብበታል

ለ. የደረሰው የሞት ጉዳት ከጥፋተኛው ሀሳብና ፍላጎት በላይ የደረሰ በመሆኑ በአስገድዶ መድፈር ወንጀል ብቻ ይከሰሳል

ሐ. መጨረሻው ሞት በመሆኑ የአጥፊው ድርጊት በአንድ ተጠቃለሎ በከባድ የሰው መግደል ወንጀል በአንድ ክስ ይከሰሳል

መ. መልስ አልተሰጠም

**27. ከሚከተሉት መካከል በዋና ወንጀል አድራጊነት እና በህብረት ስለሚፈጸም ወንጀል ተካፋይነት መርሆዎች ልዩነት የሆነው የቱ ነው?**

ሀ. በህብረት በተፈጸመ ወንጀል ውስጥ የነበረ ሰው የማይቀጣው በህብረቱ ተካፋይ አለመሆኑን ራሱ በማስረጃ ለማስረዳት ከቻለ ብቻ ነው

ለ. በህብረት የተፈጸመ ወንጀል ውስጥ ተካፋይ የሆነ ሰው የሚቀጣው ተካፋይነቱን ዐቃቤ ህግ በማስረጃ ማረጋገጥ ከቻለ ነው

ሐ. በህብረት በተፈጸመ ወንጀል ውስጥ ተካፋይ ሆነ ለማለት የወንጀሉ አድራጊዎች ቁጥር ከአንድ በላይ መሆን አለበት

መ. በወንጀል ህግ ከግምት በሚገቡ ልዩ ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር በህብረት በሚፈፀሙ ወንጀሎች ጉዳይ የዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይነት መርሆዎች ተፈፃሚ ናቸው፡፡

ሠ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው፡፡

ረ. ከ ሐ በስተቀር መልስ ናቸው፡፡

ሰ. መልስ አልተሰጠም፡፡

**28. በኢፌዴሪ ህገ መንግስትና በሀገራችን የወንጀል ህግ መሰረት በሰብዓዊነት ላይ የሚፈጸሙ እንደ ዘር ማጥፋትና የጦርነት ወንጀሎችን የፈጸመ ወንጀለኛ ላይ ተፈጻሚነት የሌለው መርህ የቱ ነው?**

ሀ. በይርጋ አይታገድም

ለ. ይቅርታ አይሰጠውም

ሐ. ምህረት አይደረግላቸውም

መ. አመክሮ አይሰጣቸውም

ሠ. ሁሉም መልስ ናቸው

**29. የዜጎችን የግላዊነት ህገመንግስታዊ መብት የሚገድቡ ልዩ የምርመራ ዘዴዎችን (ለምሳሌ የግል ስልክ ግንኙነትን በመጥለፍ) በመጠቀም የተሰበሰበ ማስረጃ በፍርድ ቤት ተቀባይነት የሚኖረው፡**

ሀ. ማስረጃውን ለመሰብሰብ በህግ የተፈቀደ ሲሆን

ለ. ማስረጃውን ለመሰብሰብ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሲኖር

ሐ. ፖሊስ የተሰጠውን የፍ/ቤት ትዕዛዝ መሰረት በማድረግ ብቻ ያገኘው ሲሆን

መ. ሁሉም ትክክል ነው

**30. የወንጀል ህግ ወደኋላ ተመልሶ የማይሰራ ስለመሆኑ በኢፌዴሪ የወንጀል ህግ የተቀመጠው መርህን በተመለከተ ትክክል የሆነው የቱ ነው?**

ሀ. የተሻሻለው የወንጀል ህግ ከመውጣቱ በፊት ለተፈጸመ የወንጀል ተግባር የተሻሻለው የወንጀል ህግ በምንም አግባብ ሊሰራ አይችልም

ለ. የተሻረው የወንጀል ህግ ይሰራ በነበረበት ጊዜ የተፈጸመ ወንጀል ሲኖር እና በአዲሱ የወንጀል ህግ ግን እንደወንጀል ያልተቆጠረ ሲሆን ሊያስከስስ አይችልም

ሐ. የተሻረው የወንጀል ህግ ይሰራ በነበረበት ጊዜ የተፈጸመ ወንጀል ሲኖር እና በአዲሱ የወንጀል ህግ ግን እንደወንጀል ያልተቆጠረ ሲሆን በዚህ ወንጀል ምክንያት አዲሱ ህግ ከመውጣቱ በፊት በቀድሞው ህግ ክስ ቀርቦባቸው የነበሩ ጉዳዮች በቀድሞው ህግ መታየታቸው ይቀጥላል

መ. ሀ እና ሐ

**31. ከሚከተሉት ውስጥ ዴሞክራሲያዊ መብቶች በሚለው ውስጥ የማይካተተው የትኛው ነው?**

ሀ. የኢኮኖሚ እድገት/የልማት መብት

ለ. የሃይማኖት መብት

ሐ. የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት

መ. የመስራት/የስራ መብት

**32. ከሚከተሉት ውስጥ የኢፌዴሪ ህገ መንግስት መሰረታዊ መርህ ያልሆነው የትኛው ነው?**

ሀ. የህዝብ ሉዓላዊነት

ለ. የህገ መንግስት የበላይነት

ሐ. የመንግስት እና የሃይማኖት መለያየት

መ. ፌዴራሊዝም

ሠ. የመንግስት አሰራር እና ተጠያቂነት

ረ. መልስ አልተሰጠም

**33. ስለኢትዮጵያ ህግ አወጣጥ ሀሰት የሆነው የቱ ነው?**

ሀ. ህግ የማውጣት ስልጣን ከላይ ወደታች (Vertically) የተከፋፈለ ነው፤

ለ. ህግ የማውጣት ስልጣን ወደጎን (Horizontally) የተከፋፈለ ነው፤

ሐ. ማንኛውም የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤት የበታች ህጎችን (Subordinate Laws) የማውጣት ስልጣን አለው፤

መ. የፌዴሬሽን ምክር ቤት ደንብ (Regulation) የማውጣት ስልጣን አለው፤

ሠ. ከ'ሀ' በስተቀር ሁሉም መልስ ናቸው፤

ረ. መልስ አልተሰጠም

**34. ከሚከተሉት ውስጥ የአክሲዮን ማህበር (SC) እና የኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር (PLC) የጋራ መገለጫ ያልሆነው:**

ሀ. የምስረታ ኦዲት (Formation Audit)

ለ. ተቆጣጣሪ ቦርድ (Supervisory Board)

ሐ. መዋሀድ (Merger)

መ. መከፋፈል (Division)

ሠ. ሀ እና ለ